# ‹‹አንድነትን አፍርሶ አንድነትን በማወጅ ሕዝብን ማታለል አይቻልም››

## (ከምርጫ 97 የቅንጅት የፓርላማ አባላት የተሰጠ መግለጫ)

የቅንጅት ለአንድነትና ለደሞክራሲ ፓርቲ ከድህረ ምርጫ በኋላ ያጋጠሙት ችግሮች መላ አባላቱንና ደጋፊውን ያሳዘኑ ክስተቶች ሆነዋል፡፡ እነዚህም መስከረም 14/1998 ዓ.ም የተፈጸመውን የውህደት ጥያቄ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አለመቀበሉ፣ የፓርቲው የአመራር አባላት ለእስር መዳረጋቸው እና የፓርቲው ጽ/ቤቶች መዘጋታቸው በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የአመራር አባላቱ ቢታሰሩም ትግሉ አይታሰርም በሚል እምነት የቅንጅት ፓርላማ እና የአዲስ አበባ ክልል ምክር ቤት አባላት ቅንጅትን በአዲስ መልክ ሚያዚያ 16/1998 ዓ.ም በማቋቋም ሕጋዊ ሰውነቱን ለማረጋገጥ ሙከራ አድርገናል፡፡ ነገር ግን ትግሉን ብቻ ሳይሆን ታጋዮቹንም አብሮ ለማሰር መጀመሪያ ላይ በአቶ ተመስገን ዘውዴና በአቶ አየለ ጫሚሶ በጋራ በኋላ ደግሞ በየቡድናቸው ያደርጉት የነበረው የፓርቲው የባለቤትነት ውዝግብ ሌላው ዙር የፓርቲው የውስጥና የውጭ ችግር ሆኖ የሕዝባችንን ስሜት የጐዳ እንቅስቃሴ ነበር፡፡

የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የአመራር አባላት ከእስር መፈታት ሕዝባችንን ያስደሰተ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ፓርቲው ቀድሞ በነበረው የአንድነት ጽናቱ ይቀጥላል ተብሎ ሲጠበቅ ጥቂት አፈንጋጮች በተሰጣቸው ፓርቲ የማፈራረስ የቤት ሥራ ድርጅቱ እንዲበተን ለማድረግ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያካሂዱ ከቆዩ በኋላ በአሁኑ ወቅት አንጃ ፈጥረው ከቅንጅት ተለይተዋል፡፡

የቅንጅት አመራሮችን የሃሳብ ልዩነት በመጠቀም የአቶ ተመስገን ዘውዴ የፓርላማ ቡድን ልዩነቱን በማስፋትና የአንጃውን ኅብረት በማጠናከር የአንድ ፓርቲ አባላት መሆናቸው እየታወቀ ተዋህደናል ብለው አወጁ፡፡

በቅንጅት አመራር የተፈጠረውን የሃሳብ ልዩነት ለመፍታት የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት አንድ ቀን እንኳ ሳይደረግ በዲሲፕሊን ግድፈት የታገዱት 5 የአመራር አባላት ጥቂት መሰሎቻቸውን በማሰባሰብ አዲስ ፓርቲ በመመስረት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ወይዘሪት ብርቱካን የፓርቲው ሊቀመንበር መሆናቸውን በይፋ መግለጻቸው መላ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎችን ያስቆጣና ያሳዘነ ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አዲስ ፓርቲ ማቋቋማቸው አላሳዘነንም፣ ይህ መብታቸው ነው፣ እኛን ከልብ ያሳዘነን ቅንጅትን

ለማዳን የምንጥር ነን ሲሉ ሰንብተው፤ ቅንጅትን በማፍረስ አዲስ ፓርቲ እየመሰረቱ ዛሬም እኛ ቅንጅት ነን፣ መሪያችን ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ናቸው በማለት ‹‹ዓይናችሁን ጨፍኑ እና እናሞኛችሁ›› የሚል የሞኞች ብሒል የቅንጅት ደጋፊ በሆነው በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በማሾፋቸው ነው፡፡ ይህ ሕዝብን የመናቅ ድርጊት እኛን የሕዝብ ተወካይ የሆነውን ብቻ ሳይሆን ስለ ዴሞክራሲ መልካም አስተያየት ያለውን ሁሉ የሚያናድድ ነው፡፡ በመሆኑም እኛ በቅንጅት ስም የተመርጥን የፓርላማ አባላት ዛሬ በጽ/ቤታችን ተገኝተን ሰሞኑኑ በእነ ወ/ሪት ብርቱካን የተመሰረተውን አዲስ ፓርቲና አጠቃላይ ሂደቱንም በሚመለከት ከዚህ በታች የተገለፀውን ባለ 7 ነጥብ የአቋም መግለጫ አውጥተናል፡፡

1. የቅንጅት ስምና የምርጫ ምልክቱ ለሌላ አካል አላግባብ ሲሰጥ በአንጃው ቡድን መሪዎች በዶ/ር ብርሃኑ ነጋና በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የሚመራው የእነ ወ/ሪት ብርቱካን ቡድን ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወስዱ ቆይተው አዲስ ፓርቲ አቋቋሙ፡፡ አዲስ ስም ሰጥቶ ፓርቲው እንዲንቀሳቀስ ማድረግ የሚቻለው ግን በጠቅላላው ጉባኤ ውሳኔ እንጂ ጥቂት የአንጃ መሪዎች ተሰባስበው በሚወስኑት ሊሆን አይችልም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት መስከረም 14 ቀን 1998 ዓ.ም የተሰበሰበውና ውኽደቱን ያፀደቀው የቀድሞው ቅንጅት ጠቅላላ ጉባኤ ሳይወስን እኛ እናውቅልሃለን በሚል ከንቱ መመጻደቅ የአንጃው ቡድን ብቻውን ተሰባስቦ የሕዝብ ትግል የወለደውን የቅንጅትን ስም ለውጦ ተከተሉኝ ማለቱ ቅንጅትን የመበተን ሴራ በመሆኑ አጠብቀን እናወግዛለን፡፡
2. የአንጃው አፈንጋጭ ቡድን አዲሱን ፓርቲ የመመስረቻ ጽሑፍና የጊዜያዊ አመራራቸውን አባላት ስም ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሲገልፁ የፓርቲው ሊቀመንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ም/ሊቀመንበር አቶ ተመስገን ዘውዴ መሆናቸውን ለመረዳት ችለናል፡፡ ይሁን እንጂ በመሰረትነው አዲስ ፓርቲ ውስጥ የእነ ኢንጅነር ኃይሉና የሌሎችም የአመራር አባላት የኃላፊነት ቦታዎች እንደተጠበቁ ናቸው በማለት ለአንዳንድ ጋዜጦች የሰጡትን መግለጫ ስናስታውስ እርስ በርሱ የሚጣረስና የቅንጅትን ሊቀመንበር ሥልጣን ያለጠቅላላ ጉባኤ ፈቃድና ውሳኔ ለመንጠቅ የተደረገ ሴራ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አፈንጋጮቹ የሕዝብ ድጋፍ ያላቸውን የፓርቲውን ሊቀመንበር አመራር የሚቀበሉ በማስመሰል የሕዝብ አመለካከት ለማደናገር የተጠቀሙበትን ሂደት በእጅጉ እንቃወማለን፡፡

3. የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ችግሮች ሲገጥሙት ሊመክርና ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው የተሟላ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባላትና በመጨረሻም የጠቅላላ ጉባኤው እንደሆነ በፓርቲው ሕገ ደንብ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ከዚህ አሠራር ባፈነገጠ መልኩ የአንጃው አባላት የማይፈልጓቸውን የቅንጅት ሥራ አስፈጻሚና የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ባገለለ ሁኔታ ከፓርቲው ጽ/ቤት ውጭ እየተሰበሰቡ የተለያዩ ውሳኔዎችን ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ አሁንም ቀጥለውበታል፡፡ እኛ የቅንጅት የፓርላማ ተመራጮች የፓርቲው የሕልውና ጉዳይ የሚመለከተን በመሆኑ አፍራሽ ድርጊታቸውን አጥብቀን እናወግዛለን፡፡

4. በቅንጅት አመራሮች መካከል የተፈጠረውን የሃሳብ ልዩነት በውይይት ከመፍታት ይልቅ አንጃ በመፍጠር በቅንጅት ዙሪያ ተሰባስቦ የነበረውን የአንድነት ኃይል ለመከፋፈል መሞከራቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ወደ ኋላ መመለስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይባስ ብለው ለቅንጅት ሲል የሞተውን፣ የቆሰለውን የተሰደደውንና ከቤት ንብረቱ የተፈናቀለውን ሕዝብ ታሪክና ማንነት በመርሳት ለነሱ ሥልጣንና ድብቅ ዓላማ ሲባል በመሠረቱት አዲስ ፓርቲ አባልነት እንዲመዘገብ ድጋሚ ጥሪ ማድረጋቸው አንድነትን አፍርሶ አንድነትን ማወጅ ሕዝብን ማታለል በመሆኑ ድርጊቱን እንቃወማለን፡፡ ስለሆነም እነ ወ/ሪት ብርቱካን ያቋቋሙት ‹‹አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ›› የሚባለው ፓርቲ ከቀድሞው የቅንጅት ፓርቲ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው በመሆኑ መላው የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች ይህንን ተረድተው እስካሁን ለቆሙለት ለቅንጅት ፓርቲ በቁርጠኝነት እንዲታገሉና በክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ከሚመራው ከእውነተኛው ቅንጅት ጐን እንዲቆሙ ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡

5. አሁን ፓርላማ ውስጥ ያለን የቅንጅት ሰዎች የተመረጥነው ቅንጅትን በ5 ዓመት ወክለን እንድንሠራ ነው፡፡ ነገር ግን ከሁሉም በላይ አሳዛኝ የሚሆነው ለ5 ዓመት በቅንጅት ስም የተመረጡ አንዳንድ የፓርላማ አባሎች የተመረጡበትን ፓርቲ ስም ከአፈንጋጮች ጋር ሆነው መለወጣቸው ነው፡፡ የፓርቲው ስም መቀየር ካለበት በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሆኑን የቅንጅት ሕገ-ደንብ ይገልጻል፡፡ ከቅንጅት የተገነጠሉ ሰዎች ግን በቅንጅት ስም ለፓርላማ የተመረጡ ጥቂት ሰዎችንም ጨምሮ በ1500 ሰዎች ፊርማ አዲስ ፓርቲ ለማቋቋም ወደ ሕዝቡ ለመሄድ በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡ አዲስ የፈጠሩትን ፓርቲ የፊርማ ድጋፍ ለማሰባሰብ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የፓርቲያችን መሪ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ናቸው በሚል ሽፋን መሆኑን ከደረሱን

መረጃዎች ተገንዝበናል። ይህ የማታለል ተግባር ደግሞ ለነሱ ተጨማሪ ወንጀል መሆኑን መረዳት አለባቸው፤ ስለሆነም የቅንጅት አባልና ደጋፊ የሆናችሁ ይህን የማስመሰልና የማጭበርበር እንቅስቃሴ አንጃዎች የፈጠሩት መሆኑን ተረድታችሁ ከጐናቸው እንዳትሰለፉ፤ ከዚህም ሌላ በቅንጅት ስም ለማወናበድ የተነሱትን በማጋለጥ ሃሳባቸው እንዳይሳካ እንድታደርጉ አደራ እንላለን።

6. የቅንጅቱ ፕሬዚዳንት ክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ከሕመማቸው በመዳናቸው የተሰማንን ደስታ እንገልጻለን። በተጨማሪም የአንጃው ቡድን ከኢትዮጵያ ውጭ በአባሎቻችን እና በደጋፊዎቻችን መካከል የፈጠረውን የመከፋፈል ሥራ ሊቀመንበራችን ዛሬ በተቃና መልኩ ለማስተካከል መቻላቸውንም እናደንቃለን። የፓርቲያችን ሊቀመንበር በአስቸኳይ ወደ አገር ቤት መጥተው በፓርቲው ዙሪያ ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሔ ለመሻት የሚችለውን የፓርቲው ከፍተኛ የሥልጣን አካል የሆነውን ጠቅላላ ጉባኤ ጠርተው ጉባኤው በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት የሕዝባችን ሰላማዊ ትግል ወደነበረበት ደረጃ እንዲመለስ እንዲያደርጉ እንጠይቃለን። እኛም በአንድነት ከሚያምኑ የፓርቲው መሪዎች ጐን በመሆን ሕዝባዊ ኃላፊነታችንን ለመወጣት ዝግጁ መሆናችንን እናረጋግጣለን። ውድ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎችም ዛሬም እንደትናንቱ ከጐናችን እንድትቆሙ ጥሪያችንን በአክብሮት እናስተላልፋለን።

7. ውድ የቅንጅት ቤተሰቦች በክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የሚመራውና መስከረም 14/1998 ዓ.ም የተዋሃደው ቅንጅት በቅርቡ ጠቅላላ ጉባኤውን ጠርቶ ያጋጠሙትን ችግሮች ሁሉ እልባት እንደሚሰጥ እናምናለን። የጠቅላላው ጉባኤ አባላት የሆናችሁ የዞንና የወረዳ ተጠሪዎች በየደረጃው ተወክላችሁ የምትመጡ የቅንጅት ቤተሰቦች ሁሉ ቅንጅትን የሚያድን ብቻ ሳይሆን በቅንጅት መሪነት ሕዝባዊ ትግሉ እንዲቀጥል የሚያደርግ ውሳኔ ከናንተ እንደሚጠበቅ ተረድታችሁ ይህንኑ ጉባኤ በንቃት እንድትጠባበቁ እየጠየቅን እኛም ከእናንተው ጋር በመሆን ጉባኤውን እውን በማድረግ ሕዝባዊ አደራችንን እንደምንወጣ ቃል እንገባለን።

ቅንጅት አንድ ነው!
መጋቢት 11/2000 ዓ.ም
አዲስ አበባ